በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ/መ/ቁ 214108

ቀን፡- 15/4 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች** ፡- ተፈሪ ገብሩ/ዶ/ር

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሣ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፡- እነ ወ/ሮ ገነት ቶላ /2 ሰዎች/ አልቀረቡም

ተጠሪ/ዎች፡- እነ አቶ ብርሃኑ ቶላ /2 ሰዎች/ 2ኛ ተጠሪ ቀረቡ

መዝገቡ ለችሎት የቀረው 2ኛ ተጠሪ ወ/ሮ ኤልሳቤት አንበርብር ህዳር 27 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በዚህ ሰበር ችሎት በክርክር ላይ የምንገኘው በጋራዥ ቤቱ ላይ ሆኖ እያለ በመኖሪያ ቤት ላይ ጨምሮ እግድ የተሰጠበት በመሆኑ ከመኖሪያ ቤቱ ላይ እግድ እንዲነሳልት ስትል አመልክታለች፡፡ የአሁን አመልካቾችም መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ታህሳስ 6 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የአፈፃፀም እግድ የተሰጠው በሚያከራክረን ንብረት ላይ በመሆኑ እግዱ ሊነሳ አይገባም ብለዋል በዚሁ መሰረት ተከታዩ ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡

## ትዕዛዝ

በዚህ መዝገብ መስከረም 10 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 162907 ላይ እግድ ተሰጥቷል፡፡ እግዱ የተሰጠው አሁን ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ወረዳ 11 የቤት ቁጥር አዲስ የሆነ አዋሳኙ በሰሜን አቶ መሀመድ፣ አቶ ገመቹ፣ አቶ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መለስ፣ በምዕራብና በምስራቅ መንገድ፣በደቡብ ከድር ሁሰኔን የሚያዋስኑት ጋራዥ ቤት ላይ ብቻ ሳይሆን የአፈፃፀም መዝገቡ ላይ በመሆኑ በሌሎች ንብረቶች ላይ እየተደረገ ያለ አፈፃፀም ካለ አፈፃፀሙን የሚከለክል መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 162907 በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ወረዳ 11 የቤት ቁጥር አዲስ የሆነ አዋሳኙ በሰሜን አቶ መሀመድ፣ አቶ ገመቹ፣ አቶ መለስ፣ በምዕራብና በምስራቅ መንገድ፣ በደቡብ ከድር ሁሰኔ የሚያዋስኑት ጋራዥ ቤት ላይ የተሰጠው የአፈፃፀም እግድ እንዲቀጥል ብለናል፡፡ በሌሎች ንብረቶች ላይ እየተደረገ ያለ አፈፃፀም ካለ በዚህ ችሎት መስከረም 10 ቀን 2014 ዓ.ም የተሰጠው እግድ ተሻሽሎ ከሌሎቹ ንብረቶች ላይ የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ መደበኛ ቀጠሮ አልተለወጠም፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም